# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو

Gaafa: 05-01-2013 تاريخ
Date:

Lakk.: 01/stm-abo/2013 رقم
No.:

## የኢትዮጵያ መንግስት በቀቢጸ-ተስፋነት የሚወስደው እርምጃ የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ይበልጥ እንዲፋፋም ይገፋፋዋል

### የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ

በፍንፍኔ ዩኒቨርሲቲ ኣራት ኪሎና ኣምስት ኪሎ ካምፓሶች የሚማሩ የኦሮሞ ተማሪዎች ከጥር 2 ቀን 2013 ጀምሮ ኣመጽ ኣቀጣጥለው እንደሚገኙ ግልጽ ነው። ቀደም ሲል ለረጂም ጊዜ ያት ሳይቋዋረጥ በመላው ኦሮምያ ሲካሄድ የቆየው የጸረ ጭቆና ኣመጽ በነዚህ የፍንፍኔ ዩኒቨርሲቲ ካምፓሶች ከተጠቀሰው እለት ጀምሮ ይበልጥ ተፋፍሟል። የወያኔ መልእክተኞች እንደ ልማዳቸው ሁሉ ዛሬም ኦሮሞና ኦሮሞነትን የሚዘልፍና የሚያንቋዋሽሽ ጽሁፍ ኣዘጋጅተው በኣራት ኪሎ ካምፓስ ውስጥ መለጠፋቸውን ተከትሎ የፈነዳው ይህ ኣመጽ ባሁኑ ወቅት ወደተቀሩት የሃገሪቷ የትምህርት ተቋዋማት እየተዛመተ መሆኑ ታውቋዋል።

ብሄራዊ ክብራቸውን ለማስጠበቅ ሲባል ኣመጹን ያቀጣጠሉት የዩኒቨርሲቲው የኦሮሞ ተማሪዎች ባሁኑ ወቅት ውድ መስዋእትነቶችን እየከፈሉ ይገኛሉ። እስካሁን የተሰባሰበው መረጃ እንደሚጠቁመው ከኣንድ መቶ በላይ የኦሮሞ ተማሪዎች ለህዝባቸው ብሄራዊ ክብር በመቆርቆራቸው ብቻ ተወንጅለው ታስረዋል። ከነዚህ ውስጥ ጥቂት የማይባሉት በደረሰባቸው ድብደባ በጽኑ ተጎድተዋል። ሌሎቹ ደግሞ የደረሱበት ኣልታወቀም። የሚዘለፈው ኦሮሞ፥ የሚታሰረው ኦሮሞ፥ የሚደበደበውም ኦሮሞ ነው።

የወያኔ መንግስት በዚህ ያረጀ የከፋፋይነት ስልቱ እየተጠቀመ በኦሮሞና በኣማራ ተማሪዎች መካከል የግጭት እሳት ሲጭር መቆየቱ የሚዘነጋ ኣይደለም። የዚህ ጸብ ኣጫሪነት ዋነኛ ኣላማም የጸረ ጭቆና ትግሉን ኣቅጣጫ ለማሳት ታስቦ መሆኑ ግልጽ ነው። የኦሮሞ ተማሪዎች በኦሮሞ ህዝብ ክብር ላይ የሚያነጣጥሩትን የዘለፋ ቃላት ለማውገዝ ባመጹ ቁጥር ኣፍሶ ማሰርና መደብደብም የስርኣቱ ባህል ሆኗል። በተለያዩ ጊዜያት የኦሮሞን ስም የሚያንቋዋሽሹ ጽሁፎች በኣንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋዋማት ውስጥ ተለጥፈው ሲገኙ እንዲህ ያሉትን ወንጀሎች የሚፈጽመውን ኣካል ተከታትሎ በቁጥጥር ስር በማዋል ተመጣጣኝ ፍርድ ያገኝ ዘንድ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የብሄራችን ክብር ለምን ይደፈራል ብለው ያመጹ የኦሮሞ ተማሪዎችን ኣፍሶ ማሰር፥ መደብደብና ከትምህርት ገበታ ማባረር የወያኔ መንግስት ልማድ ነው። እንዲህ ያለው ሆን ብሎ ኦሮሞን እያስዘለፉ መልሶ ኦሮሞውን የማጥቃቱ እርምጃ የዚህ መንግስት ጠላታዊነት በገሃድ ከሚያጋልጡ ምሳሌዎች ኣንዱና ዋነኛው ነው።

በሃገሪቷ ከፍተኛ የትምህርት ተቋዋማት፥ ኮሌጆችና ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የኦሮሞ ተማሪዎች እንዲሁም ወጣቶችና ማናቸውም የህብረተሰቡ ክፍሎች የፍንፍኔ ዩኒቨርሲቲ የኦሮሞ ተማሪዎች ያቀጣጠሉትን ኣመጽ ተቀላቅለው ለህዝባቸው ብሄራዊ ክብርና የሃገር ባለቤትነት መብታቸው መታገል ይጠበቅባቸዋል። የወያኔ መንግስት በመልእክተኞቹ ኣማካኝነት የኦሮሞን ስም እያንቋዋሸሸ መልሶ ኦሮሞን በማጥቃት ስልቱ መቀጠል እንደማይችልም ሊነገረው ይገባል።

የወያኔ መንግስት ኦሮሞና ኦሮሞነትን ለማዋረድ የሚፈጽማቸውን ተንኮሎች ሁሉ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በጽኑ ያወግዛል። ለዚህ እርምጃውም ተመጣጣኝ የሆነ ምላሽ ይሰጠዋል። እንደዚህ ያለው

ተግባር ስርኣቱን ለማስወገድ እየተካሄደ ያለውን ፍትሃዊ ትግል ይበልጥ ኣፋፋሞ የስርኣቱን የስልጣን እድሜ የሚያሳጥር መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን። እርምጃው የኦሮሞን ህዝብ ቅስም ሰብሮ የሚያንበረክከው ሳይሆን ይበልጥ ለብሄራዊ ክብሩ ዘብ እንዲቆም የሚያነሳሳው መሆኑን ወያኔዎች መገንዘብ ኣለባቸው።

በብሄራዊ ክብራቸው ላይ ያነጣጠረውን ጥቃት ለመቀልበስ ሲሉ በማመጻቸው ብቻ ተወንጀለው የታሰሩ ሁሉም ተማሪዎች ባስቸኩዋይ እንዲፈቱና በደረሰባቸው ድብደባ ምክንያት ኣካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት የደረሰባቸውም ባስቸኩዋይ ተገቢውን የህክምና ኣገልግሎትና የሞራል ካሳ እንዲያገኙ እናሳስባለን። የኦሮሞን ህዝብ ብሄራዊ ክብር ለማዋረድ ያለመውን ጽሁፍ ኣዘጋጅቶ የለጠፈ ኣካልም ባስቸኩዋይ ለፍርድ ቀርቦ ከወንጀሉ ክብደት ጋር የሚመጣጠን ብይን ሊሰጠው እንደሚገባ እናሳስባለን።

የኦሮሞ ህዝብ እጅ ለእጅ ተያይዞ በመታገል ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ብሄራዊ መብቱንና ክብሩን ማረጋገጥ እንዳለበት ጥሪ እናቀርባለን።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር

ጥር 5 ቀን 2013